# የክቡር ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛውን ዕለተ ዕረፍትን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ

ከመንገሻ መልኬ

ጠይም ዘለግ ያለ ይግዛው የተከለው
ቤቱ ቀዘቀዘ ጠወለገ ግቢው
ሕብር ቀለማሙ ሲረግፍ አበባው።

ኢትዮጵያን የሚወድ የታሪክ ምስክር
ቅኔ ሰምና ወርቅ ምስጢር የሚያበጥር
ያን ሁሉ ሊቃውንት ፈትኖ ሲቀጥር
አበባው ጎንደሬ ተነሳ ተናገር።

ብሉይና ሐዲስ በቅኔ የሚገራ
ማማው ደብረ ታቦር ደራና ፎገራ
አበባው ጎንደሬ ሰሜን ጃናሞራ።

ካባና ትከሻ ሙያና ተግባር
ተናግሮ የሚረታ ብቃት ያለው መምህር
አንደበተ ርቱዕ ቅኔ መስተጻምር
በአበባው ነበረ ጉባዔው የሚያምር።

ቅኔ ቤት አልገባሁ ቤትም አልመታልኝ
አኮኑ እንዳልለው አምጣነ ቀረብኝ
አበባው ተነሳ በስመ አብ ተቀኘልኝ።

ሀገሬን ሀገሬን እንዳለ እንደናፈቃት
አበባው ሳይጠጣ ቀረ ውሃ ጠምቶት
የአባይ፣ የተከዜ፣ የጣና ባለቤት።

ፈትኖ ሲያሳልፍ ያን ሁሉ ሊቃውንት
በሞት ተሸንፎ ትላንትና ሌሊት
አበባው ወደቀ ተኛ ወደ መሬት።

ሀገሩን የሚወድ አንድነት በአንድ ላይ
በደም የወረሰው የአጥንቱ ክፋይ
ብልህ ሰው መካሪ አርቆ አስተዋይ
የማይነቃነቅ ላመነበት ጉዳይ
ወንበሩ አነሰና አበባው መሬት ላይ።

ማማው ደብረ ታቦር የአለቃ ተክሌ ሀገር

እንደ አበባው ያለ ታላቅ ሰው ሲቀበር

ሰው እንዳይጠፋብህ ቅኔ የሚነግር።

እንዴት ያሳዝናል ሰው ሆኖ መፈጠር

ከአፈር የተሰራ ተመልሶ ከአፈር

ሊቀ ማዕምራን አበባው ሲሰበር።

መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት

ታላላቁ ቦታ አድባራት ገዳማት

ሙያ ችሎታህን በቅርቡ የሚያውቁት

እንዴት ያሳታውስህ ያ ሁሉ ሊቃውንት

ሲሰማ መርዶውን የአበባውን ዕረፍት።

ማማው ደብረ ታቦር ሀገሩ እራስ ጋይንት

ድጓ የሚያስተምረው እየጠጣ ወተት

የባለ ርስት ልጅ የባለ መሬት

አበባው እረግፎ ቀረ በስደት።

አንበሳው ተኝቶ ዝንቦች ወረውታል

ነብር የነበረው እንደ ድመት ሆንዋል

ያንን አንደበቱን ጉንፋን ከርክሮታል

ጎብረ ቀለማሙ አበባው አበባው ረግፏል።

ሀዘንና ደስታ ተፈራራቂ ነው

ደሜ ደሜ ተብሎ እንደተዘፈነው

እኔም ተቀብዩ እስቲ ላቀንቅነው

ጎብረ ቀለማሙ አበባው ደሜ ነው።

ጎብረ ቀለማሙ ጠቢቡ አበባው

በመወድስ ቅኔ እንዳመሰገንከው

ጌታችን ነፍስህን በገነት ያኑረው

ከመላእክት ጋር ድምጽህን አሰማው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ጥቅምት 2005 ዓ.ም

ለንደን